የተደነቀችና የከበረች ፈቃድህን ያለ ማቋረጥና ያለመከልከል እንዲሠሩ ያንተ ይሆኑ ዘንድ፤ የጸሎትን ቤት ፤ የንጽሕናንም ቤት የበረከትንም ቤት ስጣቸው።

Grant that they maybe Yours that without slothfulness or hindrance they may do Your Holy and blessed will, a house of prayer, a house purity and a house of blessing.

ጸግወነ እግዚኦ ለነኒ ለአግብርቲከ ወለእለ ይመጽኡ እምድኅሬነ እስከ ለዓለም መዋዕለ ጸጉ። ተንሥእ እግዚኦ አምላኪየ ወይዘረዉ ፀርከ ወይጐየዩ ኵሎሙ እምቅድመ ገጽከ እለ ይጸልዑ ቅዱሰ ወቡሩከ ስመከ።

ለእኛም ለአገልጋዮችህ ከኛም በኋላ ለሚነሡ ፤ አቤቱ ስጠን። እስከ ዘለዓለምም ዘመንን ስጥ። አቤቱ አምላኬ ሆይ ተነሥ ጠላቶችህም ይበተኑ ፤ ቅዱስ ምስጉን የሚሆን ስምህን የሚጠሉ ሁሉም ከፊትህ ይሽሹ።

Give us also, Lord, us Your servants, and to them that shall come after us, vouchsafe us to the end of the world, length of days. Arise, Lord my God, and let Your enemies be scattered, and let them that hate Your Holy and blessed name flee before You.

ወሕዝብከሰ ይኩኑ ቡሩካነ በበረከተ አእላፈ አእላፋት ወትእልፊተ አእላፋት እለ ይገብሩ ፈቃደከ ለዝሉፉ በኵሉ ጊዜ።

በጊዜው ሁሉ ፈቃድህን የሚሠሩ ወገኖችህ ግን እልፍ አእላፋት ትእልፊተ አእላፋት በሚሆኑ መላእክት በረከት የተባረኩ ይሁኑ።

But let Your people who do Your will at all times be blessed with blessings a thousand thousands and ten thousand times

በ፩ዱ ወልድከ ዘቦቱ ለከ ምስሌሁ ወምስለ ቅዱስ መንፈስ ስብሐት ወእኂዝ ይእዜኒ ወዘልፈኒ ወለዓለመ ዓለም አሜን።

ባንድ ልጅህ በርሱ ያለ ክብር ጽንዕ ለአንተ ይገባል ፤ ከእርሱ ጋራ ከመንፈስ ቅዱስም ጋራ ዛሬም ዘወትርም ለዘለዓለሙ፤ አሜን።

ten thousand through Your only-begotten Son through whom to You with Him and with the Holy Spirit be glory and dominion, both now and ever and world without end, Amen.

## ዲያቆን (Deacon)

ንበል ኵልነ በጥበበ እግዚአብሔር ጸሎተ ሃይማኖት።

በእግዚአብሔር ጥበብ ሁነን ሁላችን የሃይማኖት ጸሎት እንበል።

Let us all say, in the wisdom of God, the prayer of faith.

ነአምን በ፩ዱ አምላክ እግዚአብሔር አብ አኃዜ ኵሉ ገባሬ ሰማያት ወምድር ዘያስተርኢ ወዘኢያስተርኢ።

ሁሉን በያዘ ሰማይንና ምድርን ÷ የሚታይና የማይታየውን በፈጠረ በአንድ አምላክ በእግዚአብሔር አብ እናምናለን።

We Believe in one God the Father almighty, maker of heaven, earth and all things visible and invisible.

ወነአምን በአሐዱ እግዚእ ኢየሱስ ክርስቶስ ወልደ አብ ዋሕድ ዘህልው ምስሌሁ እምቅድመ ይትፈጠር ዓለም። ብርሃን ዘእምብርሃን አምላክ ዘእምአምላክ ዘበአማን።

ዓለም ሳይፈጠር ከእርሱ ጋራ በነበረ የአብ አንድ ልጅ በሚሆን በአንድ ጌታ በኢየሱስ ክርስቶስም እናምናለን። ከብርሃን የተገኘ ብርሃን ፤ ከእውነተኛ አምላክ የተገኘ አምላክ ፤

And we believe in one Lord Jesus Christ, the only-begotten Son of the Father who was with Him before the creation of the world: Light from light, true God from true God,

ዘተወልደ ወአኮ ዘተገብረ ዘዕሩይ ምስለ አብ በመለኮቱ ፧ ዘቦቱ ኵሉ ኮነ ወዘእንበሌሁሰ አልቦ ዘኮነ ወኢምንትኒ ዘበሰማይኒ ወዘበምድርኒ።

የተፈጠረ ያይደለ የተወለደ በመለኮቱ ከአብ ጋር የሚተካከል። ሁሉ በርሱ የሆነ ፧ በሰማይ ካለው በምድርም ካለው ያለ እርሱ ምንም ምን የሆነ የለም።

begotten not made, of one essence with His Father: All things were made by Him, and without Him nothing whatsoever was made, in Heavens or on Earth.

ዘበእንቲአነ ለሰብእ ወበእንተ መድኃኒትነ ወረደ እምሰማያት። ተሰብአ ወተሠገወ እመንፈስ ቅዱስ ወእማርያም እምቅድስት ድንግል ኮነ ብእሴ

ስለእኛ ስለሰው ስለመዳናችን ከሰማይ ወረደ። ከመንፈስ ቅዱስ የተነሣ ከቅድስት ድንግል ማርያምም ፈጽሞ ሰው ሆነ።

Who for us men and for our salivation came down from heaven, was made man and was incarnate from the Holy Spirit and from the Holy Virgin Mary. Became man,

ወተሰቅለ በእንቲአነ በመዋዕለ ጲላጦስ ጴንጤናዊ። ሐመ ወሞተ ወተቀብረ ወተንሥአ እሙታን አመ ሣልስት ዕለት በከመ ጽሑፍ ውስተ ቅዱሳት መጻሕፍት። ዐርገ በስብሐት

ሰው ሆኖ በጴንጤናዊ በጲላጦስ ዘመን ስለ እኛ ተሰቀለ ፤ ታመመ ፤ ሞተ ፤ ተቀበረም። በሦስተኛውም ቀን ከሙታን ተለይቶ ተነሣ። በቅዱሳት መጻሕፍት እንደተጻፈ በክብር ወደ ሰማይ አረገ ፤

was crucified for our sakes in the days of Pontius Pilate, suffered, died, was buried and rose from the dead on the third day as was written in the Holy scriptures: Ascended in glory into heaven,

ውስተ ሰማያት ወነበረ በየማነ አቡሁ ዳግመ ይመጽእ በስብሐት ይኰንን ሕያዋነ ወሙታነ ወአልቦ ማኅለቅት ለመንግሥቱ።

በአባቱ ቀኝ ተቀመጠ። ዳግመኛ ሕያዋንን ሙታንንም ይገዛ ዘንድ በጌትነት ይመጣል። ለመንግሥቱም ፍጻሜ የለውም።

sat at the right hand of His Father, and will come again in glory to judge the living and the dead; there is no end of His reign.

ወነአምን በመንፈስ ቅዱስ እግዚእ ማሕየዊ ዘሠረፀ እምአብ ንስግድ ሎቱ ወንሰብሖ ምስለ አብ ወወልድ ዘነበበ በነቢያት።

ጌታ ማሕየዊ በሚሆን ከአብ በሠረፀ በመንፈስ ቅዱስም እናምናለን። እንሰግድለት እናመሰግነውም ዘንድ ከአብና ከወልድ ጋራ በነቢያት የተናገረ።

And we believe in the Holy Spirit, the life- giving God, who proceeds from the Father; we worship and glorify Him with the Father and the Son; who spoke by the prophets;

ወነአምን በአሐቲ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን እንተ ላዕለ ኵሉ ጉባኤ ዘሐዋርያት። ወነአምን በአሐቲ ጥምቀት ለሥርየተ ኃጢአት።

ከሁሉ በላይ በምትሆን ሐዋርያት በሰበሰቧት በአንዲት ቅድስት ቤተ ክርስቲያንም እናምናለን። ኃጢአትን ለማስተሥረይ በአንዲት ጥምቀት እናምናለን።

And we believe in One Holy, universal, apostolic church; And we believe in One baptism for the remission of sins,

ወንሴፎ ትንሣኤ ሙታን ወሕይወተ ዘይመጽእ ለዓለመ ዓለም አሜን።

የሙታንንም መነሣት ተስፋ እናደርጋለን ፤ የሚመጣውንም ሕይወት ለዘለዓለሙ አሜን።

and wait for the resurrection from the dead and the life to come, world without end. Amen!

ካህን (Priest)

ዘኮነ ንጹሐ ይንሣእ እምቊርባን ፤ ወዘኢኮነ ንጹሐ ኢይንሣእ ከመ ኢየዐይ በእሳተ መለኮት ዘተደለወ ለሰይጣን ወለመላእክቲሁ።

ንጹሕ የሆነ ከቊርባኑ ይቀበል ፤ ንጹሕ ያልሆነ ግን አይቀበል ፤ ለሰይጣንና ለመላክተኞቹ በተዘጋጀ በመለኮት እሳት እዳይቃጠል።

He that is pure let him receive of oblation and he that is not pure let him not receive it, that he may not be consumed by the fire of the godhead which is prepared for the devil and his angles.

ዘቦ ቂም ውስተ ልቡ ወዘቦ ውስቴቱ ሕሊና ነኪር ወዝሙት ኢይቅረብ። በከመ አንጻሕኩ እደውየ እምርስሐት አፋአዊ ከማሁ ንጹሕ አነ እምደመ ኵልክሙ።

በልቡናው ቂምን የያዘ ፤ ልዩ አሳብና ዝሙትም ያለበት ቢኖር አይቅረብ። እጄን ከአፍአዊ እድፍ ንጹሕ እንዳደረግሁ እንደዚሁም ከሁላችሁ ደም ንጹሕ ነኝ።

Whosoever has revenge in his heart and who ever has in him strange thoughts and fornication let him not draw near. As I have cleansed my hands from outward pollution, so also I am pure from the blood of you all.

በድፍረትክሙ ለእመ ቀረብክሙ ኀበ ሥጋሁ ወደሙ ለክርስቶስ አልቦ ላዕሌየ ትኅላፍ ለተመጥዎትክሙ እምኔሁ። ንጹሕ አነ እምጌጋይክሙ ዳዕሙ ኃጢአትክሙ ይገብእ ዲበ ርእስክሙ ለእመ በንጹሕ ኢቀረብክሙ።

ደፍራችሁ ወደ ክርስቶስ ሥጋና ደም ብትቀርቡ ከርሱ ለመቀበላችሁ መተላለፍ የለብኝም ፤ ኃጢአታችሁ በራሳችሁ ይመለሳል እንጅ። በንጽሕና ሆናችሁ ባትቀርቡ እኔ ከበደላችሁ ንጹሕ ነኝ።

If you presumptuously draw near to the body and blood of Christ I will not be responsible for your reception thereof. I am pure of your wickedness, but your sin will return upon yourself if you do not draw nigh in purity.

## ዲያቆን (Deacon)

እመቦ ዘአስተሐቀረ ዘንተ ቃለ ቀሲስ ፤ አው ዘሰሐቀ ወዘተናገረ፤ አው ዘቆመ በእከይ ውስተ ቤተ ክርስቲያን ለያእምር ወይጠይቅ ከመ አምዕዖ ለእግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ ወአንሰሐስሐ ላዕሌሁ

ይህንን የካህኑን ቃል ያቃለለ ፤ ወይም የሳቀና የተነጋገረ ፤ ወይም በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በክፋት የቆመ ቢኖር ፤ ጌታችንንና መድኃኒታችንን ኢየሱስ ክርስቶስን እንዳሳዘነው ፤

If there is any who disdains this word of the priest or laughs or speaks or stands in the church in an evil manner, let him Know and understand that he is provoking to wraith our Lord Jesus Christ.

ህይንተ ቡራኬ መርገመ ፤ ወህይንተ ሥርየተ ኃጢአት እሳተ ገሃነም ይረክብ እምኀበ እግዚአብሔር።

በርሱም እንደተነሣሣ ይወቅ ይረዳ። ስለ በረከት ፋንታ መርገምን ፤ ስለ ኃጢአት ሥርየት ፋንታም ገሃነመ እሳትን ከእግዚአብሔር ዘንድ ይቀበላል።

and bringing upon himself a curse instead of a blessing, and will get from God the fire of hell instead of the remission of sin.

ካህን(priest)

ኦ እግዚእየ ወአምላኪየ ገባሬ ሥርዓት ወሃቤ ሰላም ወፍቅር አሰስል እምላዕሌየ ኵሎ ሕሊና እኩየ ቂመ ወቅንዓተ ወኵሎ ፍትወታተ ሥጋውያተ ወክፍለኒ እደመር

አቤቱ ጌታዬ አምላኬ ሆይ ሥርዓትን የሠራህ ሰላምንና ፍቅርን የምትሰጥ ክፉውን ሕሊና ሁሉ ቂምን ቅንዓትንም ሥጋዊ ፈቃድንም ሁሉ ከኔ አርቅልኝ።

O my Lord and my God, author of the Law, giver of peace and love, take away from me every evil thought, revenge, envy, and all the lusts of the flesh.

ምስለ አግብርቲከ ቅዱሳን እለ አሠመሩከ በሠነ ሕይወቶሙ በመዋዕለ ፍቅር ወሰላም ፤ እስመ አንተ ውእቱ ዘወረድከ እምሰማይ ወገበርከ ሰላመ ምስለ ሰማያውያን ወምድራውያን

በበጎ ሕይወታቸው በሰላምና በፍቅር ወራት ካገለገሉህ ከክቡራን አገልጋዮችህ ጋራ አንድ እንድሆን አድለኝ። ከሰማይ የወረድህ ከሰማያውያንና ከምድራውያን ጋራ ሰላምን ያደረግህ።

Make me meet to be added to Your Holy servants who pleased You by the beauty of their lives in the days of love and peace፡ Because it is You who did come down from heaven and make peace between the inhabitants of heaven and the inhabitants of earth,

ወአስተጋባእኮሙ ለኵሎሙ ሕዝብከ ከመ ይሰብሑ ኪያከ እስመ ለከ ስብሐት ለዓለመ ዓለም አሜን።

አንተንም ያመሰግኑ ዘንድ ወገኖችህንም ሁሉ የሰበሰብሃቸው አንተ ነህና ምስጋና የሚገባህ ስለ ሆነ ለዘለዓለሙ አሜን።

and did gather together all Your people to glorify You, for Yours is the glory, world without end. Amen.

**ዲይቆን (Deacon)**

ተንሥኡ ለጸሎት።

ለጸሎት ተነሡ።

Stand up for prayer.

**ሕዝብ (People)**

እግዚኦ ተሣሃለነ።

አቤቱ ይቅር በለን።

Lord have mercy upon us.

**ካህን (Priest)**

ሰላም ለኵልክሙ።

ሰላም ለሁላችሁ ይሁን።

Peace be unto you all.

**ሕዝብ (People)**

ምስለ መንፈስከ።

ከመንፈስህ ጋራ።

And with Your spirit.

# ጸሎተ አምኃ ዘባስልዮስ

## ባስልዮስ የተናገረው የስጦታ ጸሎት

## Prayer of Salutation Basil

ካህን (Priest)

እግዚአብሔር ዐቢይ ዘለዓለም ዘለሐኮ ለሰብእ እንበለ ሙስና።

ለዘላለሙ ገናና የምትሆን እግዚአብሔር ሆይ ፣ ያለጥፋት ሰውን የፈጠርኸው ፤

God, great eternal, Who did form man uncorrupt,

ሞተ ዘቦአ ቀዳሚ በቅንዓተ ሰይጣን አብጠልከ በምጽአቱ ለሕያው ወልድከ እግዚእነ ወአምላክነ ወመድኃኒነ ኢየሱስ ክርስቶስ።

አስቀድሞ በሰይጣን ቅንዓት የገባውን ሞት ሕያው በሚሆን ልጅህ በጌታችንና በአምላካችን በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ መምጣት አጠፋህ።

You did abolish death that came first through the envy of Satan, by the advent of Your living Son our Lord, and our God, and Saviour Jesus Christ,

ወመላዕከ ኵላ ምድረ ሰላመከ እንተ እምሰማያት እንተ ባቲ ሠራዊተ ሰማያት ይሴብሑከ እንዘ ይብሉ ስብሐት ለእግዚአብሔር በሰማያት ፤ ወሰላም በምድር ሥምረቱ ለሰብእ።

የሰማይ ሠራዊት እንዲህ እያሉ አንተን ያመሰገኑባትን ከሰማይ የተገኘች ሰላምን በምድር ሁሉ መላህ። "በሰማይ ለእግዚአብሔር ምሥጋና ይገባል ፤ በምድርም ሰላም የሰው ፈቃድ።"

and You did fill all the earth with Your peace which is from heaven wherein the armies of heaven glorify You saying : "Glory to God in heaven and on earth peace, His goodwill toward men."

**ሕዝብ (People)**

ስብሐት ለእግዚአብሔር በሰማያት ፤ ወሰላም በምድር ሥምረቱ ለሰብእ።

በሰማይ ለእግዚአብሔር ምስጋና ይገባል። በምድርም ሰላም ፤ የሰው ፈቃድ።

Glory to God in heaven and on earth peace, His goodwill toward men.

ካህን(priest)

ኦ እግዚኦ በሥምረትከ ምላዕ ውስተ አልባቢነ ለኵልነ ወአንጽሐነ እምኵሉ ደነስ ወእምኵሉ ምርዓት ፤ ወእምኵሉ ቂም ወቅንዓት ፤ ወእምኵሉ ምግባር ሕሱም ወእምተዘክሮ እኪይ እንተ ታለብስ ሞተ።

አቤቱ ፈቃድህን በሁላችን ልቡና ሙላ ፤ ከኃጢአትም ሁሉ ከጽርዓትም ሁሉ አንጻን። ከቂምና ከቅንዓት ሁሉ ፤ ከክፉም ሥራ ሁሉ ሞትን ከምታለብስ ክፉን ነገር ከማሰብ አንጻን።

O Lord, in Your Goodwill fill the hearts of us all and purify us from all corruption and from all excess, and from all revenge and envy, and from all wrongdoing and from the remembrance of ill which clothes with death.

ወረስየነ ለኵልነ ድልዋነ ከመ ንትአማኅ በበይናቲነ በአምኃ ቅድሳት።

በተለየች እማኄ እርስ በርሳችን እጅ እንነሳ ዘንድ ሁላችንንም የበቃን አድርገን።

And make us all meet to salute one another with a Holy salutation.

ዲያቆን (Deacon)

ጸልዩ በእንተ ሰላም ፍጽምት ወፍቅር ተአምኁ በበይናቲክሙ በአምኃ ቅድሳት።

ፍጽምት ስለምትሆን ሰላምና ፍቅር ጸልዩ። እርስ በእርሳችሁ በተለየች ሰላምታ እጅ ተነሣሡ።

Pray for the perfect peace and love. Salute one another with a Holy salutation.

**ሕዝብ (People)**

ክርስቶስ አምላክነ ረስየነ ድልዋነ ከመ ንትአማኅ በበይናቲነ በአምኃ ቅድሳት።

አምላካችን ክርስቶስ ሆይ እርስ በርሳችን በተለየች ሰላምታ እጅ እንነሣሣ ዘንድ የበቃን አድርገን።

Christ our God, make us meet to salute one another with Holy salutation.

ካህን (Priest)

ወንትመጠ እንበለ ኰነኔ እምሀብትከ ቅድስት እንተ ይእቲ እንበለ ሞት ሰማያዊት በኢየሱስ ክርስቶስ እግዚእነ።

ክብርት ከምትሆን ስጦታህ ሳይፈረድብን እንቀበል። ይህችውም የማታልፍ ሰማያዊት ናት።

And to partake, without condemnation, of Your Holy immortal heavenly gift, through Jesus Christ our Lord:

ዘቦቱ ለከ ምስሌሁ ወምስለ ቅዱስ መንፈስ ስብሐት ወእኂዝ ይእዜኒ ወዘልፈኒ ወለዓለመ ዓለም አሜን።

በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ በእርሱ ያለ ክብር ጽንዕ ፤ ከርሱ ጋራ ከመንፈስ ቅዱስ ጋራ ለአንተ ምስጋና ይገባል ዛሬም ዘወትርም ለዘላለሙ አሜን።

Through whom to You with Him and with the Holy Spirit be glory and dominion, both now and ever and world without end. Amen.

# ቅዳሴ ዮሐንስ አፈወርቅ መጀመሪያ
# The Anaphora Of John Chrysostom Stars

ካህን (Priest)

አኮቴተ ቁርባን ዘቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ጸሎቱ ወበረከቱ የሃሉ ምስለ ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳቲነ .........ወምስለ ሊቀ ጳጳስነ........ ወምስለ ኵልነ ሕዝበ ክርስቲያን ወይዕቀባ ለሀገሪትነ ኢትዮጵያ ለዓለመ ዓለም አሜን።

የቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ የቁርባን ምስጋና። ጸሎቱና በረከቱ ከጳጳሳቱ አለቃ .......ና በጳጳሳችን.......... ከሁላችንም ጋራ ይሁን ፤ አገራችንን ኢትዮጵያንም ይጠብቃት ለዘላለሙ አሜን።

The Anaphora of Saint John Chrysostom, may his prayer and blessing be with our Patriarch and Our Bishop, and may He watch over Ethiopia, world without end. Amen.

ካህን (Priest)

እግዚአብሔር ምስለ ኵልክሙ።

እግዚአብሔር ከሁላችሁም ጋር ይሁን።

The Lord be with you all.

ሕዝብ (People)

ምስለ መንፈስከ።

ከመንፈስህ ጋራ።

And with Your spirit.

ካህን (Priest)

አእኵትዎ ለአምላክነ።

አምላካችንን አመስግኑት።

Give thanks unto our God.

ሕዝብ (People)

ርቱዕ ይደሉ።

እውነት ነው ይገባዋል።

It is right, it is just.

ካህን (Priest)

አልዕሉ አልባቢክሙ።

ልቡናችሁ ሰማያዊ ነገርን ያስብ።

Lift up your hearts.

ሕዝብ (People)

ብነ ኀበ እግዚአብሔር አምላክነ።

በአምላካችን በእግዚአብሔር ዘንድ አለን።

We have lifted them up unto the Lord our God.

# ቡራኬ

# Benediction

ዲያቆን (Deacon)

ላዕለ ይኩን ኅሊናክሙ ፤ በሰማይ የሃሉ ልብክሙ ፤ አእምሩ ኀበ ዘትትቀውሙ ፤ ወስምዑ ቃለ ጽድቅ ፤ ወአጽምዑ ዜና ሠናየ።

ኅሊናችሁ ወደ ላይ ይሁን። ልቡናችሁም በሰማይ ይኑር። የምትቆሙበትን ዕወቁ። የጽድቅንም ቃል ስሙ። በጎ ነገርንም አድምጡ።

Let your thought be above, and your heart in heaven, recognize where you stand ; hear the word of righteousness and listen to the good news.

ካህን (Priest)

ናሁ ንዜኑ ህላዌሁ ለአብ ዘሀሎ እምቅድመ ይትፈጠር ዓለም ወይሄሉ እስከ ለዓለም። አልቦ እምቅድሜሁ ፤ ወአልቦ እምድኅሬሁ ወአልቦ ዘከማሁ ወአልቦ የአምር ዘከመ እፎ ውእቱ።

ዓለም ሳይፈጠር የነበረው ለዘላለምም የሚኖር የአብን አነዋወሩን እነሆ እንናገራለን። ከእርሱ አስቀድሞ የለም። ከርሱም በኋላ የለም። እንደርሱ ያለ የለም። እንደምንም እንደሆነ የሚያውቅ የለም።

Behold we proclaim the existence of the Father Who was before the world was created and will live for ever. None was before Him, none will be after Him, none is like Him, and none knows what is His being.

ዘውእቱ ህልው እምቅድመ ኵሉ እምቅድመ ይትረበባ ሰማያት ወእምቅድመ ያስተርኢ ገጸ የብስ ፤ እምቅድመ ይቁሙ አድባራት ፤ ወእምቅድመ ይትረገወ ኑኀ አየራት ህልው ውእቱ በህላዌሁ።

እርሱ ከሁሉ አስቀድሞ የነበረ ነው። ሰማያት ሳይዘረጉ ፤ የየብሱ ፊት ሳይታይ ፤ ተራሮች ሳይቆሙ ፤ የአየር ርዝመት ሳይከፈት በባሕርዩ የነበረ ነው።

He who was before all, before the heavens were stretched out, before the face of the earth appeared, before the mountains arose, before the airs expanded He was in His place.

እምቅድመ ይዕምቁ ቀላያት ፤ ወእምቅድመ ይፍልሑ አንቅዕተ ማያት ፤ ወእምቅድመ ያንበሐብሐ ወሐይዝተ አፍላግ ህልው ውእቱ በህላዌሁ።

ቀላያት ጥልቅ ሳይሆኑ ፤ የወንዞም ጎርፎች ሳይፈሱ በባሕርዩ የነበረ ነው።

Before the depths were established and the floods began to flow as rivers, He was in His place.

እምቅድመ ይነፍሑ ነፋሳት ፤ ወእምቅድመ ያንበስብስ ፀዓዕ እምቅድመ ይትመልኍ መባርቅት ፤ ወእምቅድመ ይድምፅ ነጐድጓድ ወእምቅድመ ይሰሐው ግዘፈ ደመናት ፤ ህልው ውእቱ በህላዌሁ።

ነፋሳት ሳይነፍሱ ፤ ብልጭልጭታውም ሳይመላለስ ፤ መባርቅት ሳይመዘዙ ፤ ነጎድጓድ ሳይሰማ ፤ የደመናትም ግዘፍ ሳይሳብ በባሕርዩ የነበረ ነው።

Before the winds blew, before the thunderbolts flashed, before the lightenings were drawn out, before the thunders thundered, and before the clouds started to spread, He was in His place.

እምቅድመ ይትጋውሁ ብርሃናት ፤ ወእምቅድመ ይንጦላዕ ጽልመት ፤ እምቅድመ ይብራህ ብርሃነ መዓልት ፤ ወእምቅድመ ይትሐደም ሌሊት ፤ ህልው ውእቱ በህላዌሁ።

ብርሃናት ሳያበሩ ፤ ጨለማ ሳይጋረድ ፤ የመዓልትም ብርሃን ሳይበራ ፤ ሌሊትም ሳይፈጠር በባሕርዩ የነበረ ነው።

Before the lights appeared, before the darkness was to cover, before the light of the day gave light, and before night was fixed, He was in His place.

እምቅድመ ይስፍን ፀሓይ በኑኀ መዓልት ፤ ወእምቅድመ ይምልክ ወርኅ በኑኀ ሌሊት ህልው ውእቱ በህላዌሁ።

ፀሓይ የመዓልትን ርዝመት ሳይገዛ ፤ ጨረቃም የሌሊትን ርዝምት ሳይገዛ ፤ በባሕርዩ የነበረ ነው።

Before the sun fixed the length of the day and before the moon fixed the length of the night, He was in His place.

እምቅድመ ይትባረጹ ከዋክብት ፤ ወእምቅድመ ይትሐወሱ መናፍስት እምቅድመ ይትፈጠሩ መላእክት ህልው ውእቱ በህላዌሁ።

ከዋክብት ሳይብለጨለጩ ፤ መናፍስትም ሳይነቃነቁ ፤ መላእክትም ሳይፈጠሩ በባሕርዩ የነበረ ነው።

Before the stars glittered, before the spirits moved, and before the angels were created, He was in His place.

እምቅድመ ነፍስ ነባቢት ወእምቅድመ ሥጋ መዋቲት ፤ እምቅድመ ኵሉ ፍጥረት ዘኅቡእ ወዘክሡት ዘመልዕልት ወዘመትሕት ህልው ውእቱ በህላዌሁ።

ከነባቢት ነፍስና ከሟች ሥጋ ፤ ከተሠወረውና ከተገለጸው በላይና በታች ካለው ፍጥረት ሁሉ ፤ አስቀድሞ በባሕርዩ የነበረ ነው።

Before the speaking soul, before the mortal flesh, and before all the creatures, those that live in hiding and those that live in the open; those that are above and those that are beneath, He was in His place.

እምቅድመ ጊዜ ወሰዓት ፤ ወእምቅድመ ለያልይ ወዕለታት ፤ ወእምቅድመ አውራኅ ወዓመታት ፤ እምቅድመ መዋዕል ወአዝማናት ህልው ውእቱ በህላዌሁ።

ከጊዜና ከሰዓት አስቀድሞ ፤ ከሌሊትና ከመዓልትም አስቀድሞ ፤ ከወርና ከዓመትም አስቀድሞ ፤ ከዕለታትና ከዘመናትም አስቀድሞ በባሕርዩ የነበረ ነው።

Before time and hours, before nights and days, before months and years before days of the week and the seasons, He was in His place.

ስብሐቲሁ ዘእምኀቤሁ ወውዳሴሁ እምዚአሁ ምሉዕ ወፍጹም ውእቱ ብዕለ ጸጋሁ።

ክብሩ ከሱ ዘንድ የተገኘ ነው። ምስጋናውም ከእርሱ የተገኘ ነው። የጸጋውም ብዕል ምሉና ፍጹም ነው።

His glory is from Himself, His praise is from Himself, and the riches of His grace are full and perfect.

ንንግር እንከ ዕበየ ምሕረቱ ዘተዐውቀ በላዕሌነ ዘኢይትኌለቍ ወዘኢይሰፈር። ወሶበ ዐለውነ ትእዛዞ በምክረ ከይሲ ርጉም ወፃእነ እምገነተ ተድላ ውስተ ሙስና እምሕይወት ውስተ ሞት

እንግዲህ የማይቆጠርና የማይሰፈር በእኛ ላይ የታወቀ የቸርነቱን ብዛት እንናገር። ርጉም በሆነ ከይሲ ምክር ትእዛዙን ባፈረስን ጊዜ ከተድላ ገነት ወደ ጥፋት ፤ ከሕይወት ወደ ሞት፤

Then let us speak of the greatness of His mercies which have appeared unto us and which cannot be counted or measured. When we transgressed His commandment through the advice of the cursed serpent we were driven from the garden of delight unto destruction, from life unto death,

እምግዕዛን ውስተ ግብርናት ወተቀነይነ ለአርዑተ ኃጢአት። ውእቱሰ ኢኀደገነ ወኢተሐየየነ ለተግባሩ ወኢትቀየመነ በኃጣውኢነ ፍጹመ በከመ አበስነ ሎቱ አላ አፍቀረነ ወሐወጸነ

ከነፃነት ወደ መገዛት መጣን ፤ ለኃጢአት ቀንበር ተገዛን። እርሱ ግን ፍጥረቶቹን አልተወንም ፤ ቸል አላለንም። እርሱን እንደ በደልነው መጠን ፈጽመን እንጠፋ ዘንድ በኃጢአታችን አልተቀየመንም ወደደን እንጂ።

from freedom unto slavery, and we submitted ourselves to the yoke of sin. But He did not forsake or neglect us, who were His workmanship, and did not take vengeance upon us because of our sins so that we should utterly perish as we committed sin against Him, but He loved us,

መሐረነ ወተሣሃለነ ወአንገፈነ እምእደ ዘይቀንየነ።

ማረን ይቅርም አለን ፤ ከሚገዛንም እጅ አዳነን።

had mercy upon us and saved us from the hand of who enslaved us.

ፈነወ ለነ ወልዶ መድኅነ ወመቤዝወ መልአከ ምክሩ የማኑ እደ መዝራዕቱ ኃይሉ ወጥበቡ ለአቡሁ። ወቦቱ ኵሎ ዘፈቀደ አለ እምውስተ ዝንቱ ዓለም።

አዳኝ ፥ መድኃኒት ፥ የምክሩ አበጋዝ ለአባቱ ቀኝ እጁ ፥ ክንዱ ኃይሉና ጥበቡ የሚሆን ልጁን ላከልን። በእርሱም ከዚህ ዓለም የወደደውን ሁሉ አደረገ።

He sent unto us his saving and redeeming Son, the messenger of His counsel, His right hand, His arm, His power, and the wisdom of His Father. Through Him He did all that He desired in this world.

ለእለ ኀረየ ኪያሆሙ ጸውዐ ፤ ወለእለ ጸውዐ ኪያሆሙ አፍቀረ ፤ ወለእለ አፍቀረ ኪያሆሙ አክበረ። ወለእለ አክበረ ኪያሆሙ አጽደቀ፤

የመረጠውን እነርሱን ጠራቸው። የጠራቸውን እነርሱንም ወደደ። የወደዳቸውንም እነርሱን አከበረ። ያከበራቸውንም እነርሱን እውነተኞች አደረገ።

Whom He did predestinate, them He called; whom He called, them He loved ; whom He loved, them He honoured ; whom He honoured, them He justified;

ወለእለ አጽደቀ ኪያሆሙ ሠርዐ ከመ ይኩኑ ትርሲተ ወልዱ። ወቦቱ አስተጋብአነ እምዝርወት ውስተ እንተ ተዐቢ ሃይማኖት ወረሰየነ ሎቱ ሕዝበ ጉቡአ ወአቅረበነ ኀቤሁ ለስባሔሁ።

እውነተኞች ያደረጋቸውን እነርሱንም አከናወነ የልጁ ጌጥ ይሆኑ ዘንድ። ከእርሱም ከመበተን ከፍ ባለች ሃይማኖት ሰበሰበን። ለእርሱ የተሰበሰበ ወገንም አደረገን። እርሱን ለማመስገን ወደእርሱ አቀረበን።

whom He justified, them He glorified to be an adornment for His Son. And through Him He gathered us to the great faith, we who were scattered, and made us to Himself a gathered people, and drew us nearer unto Himself to glorify Him.

ወጸሐፈ አስማቲነ ውስተ መጽሐፈ ሕይወት ከመ ይኩን ትዝካሮሙ በቅድሜሁ ለለ አሐዱ አሐዱ ለሙታን ወለሕያዋን።

ስማችንንም በሕይወት መጽሐፍ ጻፈ። የሙታንም የሕያዋንም መታሰቢያቸው በየእያንዳንዳቸው በፊቱ ይሆን ዘንድ

He wrote our names in the book of life so that the remembrance of every one, the dead and the living, might before Him.

ዲያቆን (Deacon)

በእንተ ብፁዕ ወቅዱስ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት አባ.............፤ ወብፁዕ ጳጳስ አባ..............................።

ብፁዕ ቅዱስ ስለሚሆን ስለ ርእሰ ጳጳሳት ስለ አባ....................
ብፁዕም ስለሚሆን ስለ አባ .........

For the sake of the blessed and holy Patriarch Abba ............. and the
blessed Archbishop Abba .....................

እንዘ የአኵቱከ በጸሎቶሙ ወበስእለቶሙ እስጢፋኖስ ቀዳሜ ሰማዕት ዘካርያስ ካህን ወዮሐንስ መጥምቅ።

በጸሎታቸውና በልመናቸው ሲያመሰግኑህ የሰማዕታት መጀመሪያ እስጢፋኖስ። ካህኑ ዘካርያስና መጥምቁ ዮሐንስ

While they yet give thee thanks in their prayer and in their supplication: Stephen the first martyr, Zacharias the priest and John the Baptist.

ወበእንተ ኵሎሙ ቅዱሳን ወሰማዕት እለ አዕረፉ በርትዕት በሃይማኖት ማቴዎስ ወማርቆስ ሊቃስ ወዮሐንስ ፬ቱ ወንጌላውያን። ማርያም ወላዲተ አምላክ። .......

በሃይማኖት ስላረፉ ስለ ቅዱሳንና ስለ ሰማዕታት ሁሉ፤ አራቱ ወንጌላውያን ማቴዎስና ማርቆስ ሉቃስና ዮሐንስ፤ አምላክን የወለደች ማርያም።.......

And for the sake of all the saints and martyrs who have gone to their rest in faith Matthew and mark, Luke and John the four Evangelist; Mary the mother of God,.......

ንፍቅ ካህን/Ass't priest/

ኦ ሥሉስ ቅዱስ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ ባርክ ዲበ ሕዝብከ ፍቁራን ክርስቶሳውያን በበረከተ ሰማያውያን ወምድራውያን ወፈኑ ላዕሌነ ጸጋ መንፈስ ቅዱስ።

ልዩ ሦስት የምትሆን አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ ሆይ የሚፋቀሩ የክርስቶስ ወገኖች የሚሆኑ ሕዝብህን በሰማያውያንና በምድራዊያን በረከት ባርክ። በእኛ ላይም የመንፈስ ቅዱስን ጸጋ ላክ።

O; Holy Trinity Father and Son and Holy Spirit, bless your people, Christians beloved, with blessings heavenly and earthly and send upon us the grace of the Holy Spirit

ወረሲ ኆዋኅወ ቤተ ክርስቲያንከ ቅድስት ርኅዋተ ለነ በምሕረት ወበአሚን ወፈጽም ለነ አሚነ ሥላሴከ ቅድስት እስከ ደኃሪት እስትንፋስ።

የቅድስት ቤተ ክርስቲያንህም ደጆች በምሕረትና በሃይማኖት እንዲከፈቱ አድርግልን እስከ መጨረሻዪቱ ሕቅታም ድረስ ልዩ ሦስትነትህን ማመንን ፈጽምልን።

and make the doors of Your Holy Church open unto us in mercy and in faith; and perfect unto us the faith of Your Holy Trinity unto our latest breath .

ኦ እግዚእየ ኢየሱስ ክርስቶስ ሐውጽ ሕሙማነ ሕዝብከ ፈውሶሙ ወምርሖሙ ለአበዊነ ወለአኀዊነ እለ ሖሩ ወተአንገዱ ወሚጦሙ ኀበ ማኅደሪሆሙ በሰላም ወበጥዒና ባርክ ነፋሳተ ሰማይ።

ጌታዬ ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ የታመሙ ወገኖችህን ጐብኝ የሄዱትንና እንግዶች የሆኑትን አባቶቻችንን ወንድሞቻችንን መርተህ በሰላምና በጤና ወደ ቤታቸው መልሳቸው። የሰማዩን ነፋስ ባርክ።

O my Lord Jesus Christ visit the sick of Your people; heal them; and guide our fathers and our brothers who have gone forth and become strangers bring them back to their dwelling places in peace and in health. Bless the airs of heaven

ወዝናማተ ወፍሬያተ ምድር ዘዛቲ ዓመት በከመ ጸጋከ ወረሲ ፍግዓ ወተድላ ወትረ ዲበ ገጸ ለምድር ወአጽንዕ ለነ ሰላመከ ሚጥ ልበ ነገሥት አዚዛን ለአሠንዮ ላዕሌነ በኵሉ ጊዜ።

ዝናሙንም በዚህች ዓመት የሚያፈራውን የምድሩን ፍሬ እንደ ቸርነትህ ባርክ ዘወትር ተድላንና ደስታን አድርግ ሰላምህንም አጽናልን ሁልጊዜ ለኛ በጎ ነገርን ሊያደርጉልን ጽኑዓን የሚሆኑ የኃያላኑን ልቡና መልስ።

and the rains and the fruits of the earth of this year, in accordance with Your grace, and make joy and gladness prevail perpetually on the face of the earth And establish for us Your peace. Turn the hearts of mighty kings to deal Kindly with us always.

ጸጉ ሰላመ ለሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን እለ ጉቡኣን ውስተ ቤተ ክርስቲን ቅድስት ኵሎ ጊዜ ለኵሉ ለለአሐዱ በበአስማቲሆሙ በቅድመ ኃያላን አምላክነ አንኅሎሙ።

በቅድስት ቤተ ክርስቲያንህ ሁል ጊዜ ለሚሰበሰቡ ለቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት ፍቅርን ስጥ ለሁሉም ለያንዳንዱ በየስማቸው ኃያላን በሚሆኑ ፊት ሰላምን አብዛላቸው፡፡

Grant peace of the scholars of the church who are continually gathered in Your Holy Church; to all, to each by their own names; in the presence of powerful kings, O our God, increase Your peace,

ወአዕርፍ ነፍሳተ አበዊነ ወአኀዊነ ወአኃቲነ እለ ኖሙ ወአዕረፉ በርትዕት ሃይማኖት።

አምላካችን ሆይ በቀናች ሃይማኖት ሆነው ያንቀላፉትንና ያረፉትን ያባቶቻችንንና የወንድሞቻችንን የእኅቶቻችንንም ነፍስ አሳርፍ።

Rest the souls of our fathers and our brothers and our fathers and our brothers and our sisters who have fallen asleep and gained their rest in the right faith.

ወባርክ ዲበ እለ ያስተነትኑ በዕጣን ወቍርባን ወወይን ወቅብዕ ወዘይት ወመንጠዋልዕ ወመጻሕፍተ ምንባባት ወንዋያተ መቅደስ ከመ ክርስቶስ አምላክነ ይዕሥዮሙ በኢየሩሳሌም ሰማያዊት፡፡

አምላካችን ክርስቶስ በኢየሩሳሌም ሰማያዊት ዋጋቸውን ይከፍላቸው ዘንድ ዕጣንና ቍርባን ወይንና ሜሮን ዘይትም መጋረጃም የንባብ መጽሐፍቶችን የቤተ መቅደስንም ንዋያት በመስጠት የሚያገለግሉትን ባርክ።

And bless those who give gifts of incense and bread and wine, and ointment and lamp oil, and hangings and reading books and vessels for the sanctuary, that Christ our God may give them their reward in the heavenly Jerusalem.

ወለኵሎሙ እለ ተጋብኡ ምስሌነ ይኅሥሡ ምሕረተ ክርስቶስ አምላክነ ተሣሃል ላዕሌሆሙ ወለኵሎሙ እለ አምጽኡ ምጽተ በቅድመ መንበርከ መፍርህ ወመደንግፅ ተወከፎሙ።

ይቅርታን ያገኙ ዘንድ ከእኛ ጋራ የተሰበሰቡትን ሁሉ አምላካችን ክርስቶስ ሆይ ይቅር በላቸው በሚያስፈራና በሚያስደነግጥ በመንበርህ ፊት ምጽዋት ያመጡትንም ሁሉ ተቀበላቸው።

And all them that are assembled with us to entreat for mercy: Christ our God have mercy upon them: and all them that give alms before Your awful and terrifying throne, receive.

ወአንኊ ለኵላ ነፍስ ዕፅብት ወእለ እሡራን በመዋቅሕት ወእለ ሀለዉ ውስተ ስደት ወፂዋዌ ወእለ እኊዛን በቅኔ መሪር አምላክነ አድኅኖሙ በምሕረትከ።

የተጨነቀችዪቱን ነፍስ ሁሉ አሳርፍ በሰንሰለት የታሰሩትን በስደትና በምርኮ ያሉትንም መሪር በሆነ አገዛዝ የተያዙትንም አምላካችን ሆይ በቸርነትህ አድናቸው።

And comfort every straitened soul, them that are in chains and them that are in exile or captivity. And them that are held in bitter servitude: our God, deliver them in Your mercy.

ኦ ሊቅነ ኢየሱስ ክርስቶስ ለኵሎሙ እለ አዘዙነ ከመ ንዘከሮሙ በጊዜ አስተብቍዖትነ ኀቤከ ተዘከሮሙ በመንግሥትከ ሰማያዊት ወሊተኒ ለኃጥእ ገብርከ ተዘከረኒ።

መምህራችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ ወዳንተ በምንማልድበት ጊዜ እንድናስባቸው ያዘዙንን ሁሉ በሰማያዊት መንግሥትህ አስባቸው፡፡ ኃጥእ ባርያህን እኔንም አስበኝ።

And all them that have entrusted it to us to remember them in our supplications to You: Our Master Jesus Christ, remember them in Your heavenly kingdom, and remember me, Your sinful servant.

ኦ እግዚኦ አድኅን ሕዝበከ ወባርክ ርስተከ። ረዓዮሙ ወአልዕሎሙ እስከ ለዓለም።

አቤቱ ሕዝብህን አድን ርስትህንም ባርክ። ጠብቃቸው እስከ ዘላለምም ከፍ ከፍ አድርጋቸው።

O Lord, save your people and bless Your inheritance feed them and lift them up for ever.

ዲያቆን (Deacon)

መሐሮሙ እግዚኦ ወተሣሃሎሙ ለሊቃነ ጳጳሳት ፤ ጳጳሳት ኤጲስ ቆጶሳት ቀሳውስት ወዲያቆናት ወሦሎሙ ሕዝበ ክርስቲያን።

አቤቱ የጳጳሳት አለቆችን ፣ ጳጳሳቱንና ኤጲስ ቆጶሳቱን ፣ ቀሳውስቱንና ዲያቆናቱን ፣ የክርስቲያን ወገኖችን ሁሉ ማራቸው ፤ ይቅርም በላቸው።

Lord pity and have mercy upon the patriarchs, archbishops, bishops, priest, deacons and all the Christian people.

ካህን(Priest)

ንዜኑ ካዕበ ህላዌሁ ለዋሕድ ዘከመ እፎ ውእቱ ፤ ወዘከመ እፎ ርደቱ ፤ ወዘከመ እፎ ልደቱ። መጽአ እንዘ ኢይወፅእ እምአቡሁ ፤ ወረደ እንዘ ኢይትፈለጥ እምህላዌሁ።

ዳግመኛ የዋሕድ አነዋወሩ እንደምን እንደሆነ ፤ መውረዱም እንዴት እንደሆነ ፤ መወለዱም እንዴት እንደሆነ እንናገራለን። ከአባቱ ሳይወጣ መጣ ፤ ከአነዋወሩ ሳይለይ ወረደ።

Again we proclaim the existence of the only-begotten, what He is, what was His descent, and what was His birth. He came without going out of His Father, He descended without removing from His position,

ነገደ እንዘ ኢይትበዐድ እምሥላሴሁ ፤ አጽነነ እንዘ ኢይዘሮ እምድማሬሁ ፤ ኅደረ ውስተ ወለተ ሥጋ እንዘ ኢየዐርቅ እመንበሩ።

ከሦስትነቱ ሳይለይ መጣ። ከአንድነቱም ሳይለይ ወረደ። ከዙፋኑ ሳይለይ በሥጋ ልጅ አደረ።

He came without being separated from the Trinity, He came down without breaking His unity and He dwelt in a daughter of flesh without leaving His throne.

ዲያቆን (Deacon)

እለ ትነብሩ ተንሥኡ።

የተቀመጣችሁ ተነሡ።

You, that are sitting, stand up.

ካህን (Priest)

ተፀንሰ በከርሥ እንዘ ኢይትጋባእ እምኵለሄ በምልዓቱ ፤ ተዐቍረ ውስተ ማኅፀን እንዘ ኢየሐጽጽ በላዕሉ ፤ ወተወልደ እንዘ ኢይትዌሰክ በታሕቱ።

ከምላቱ ሳይወሰን በማኅፀን ተፀነሰ። በላይ ሳይጎድል በማኅፀን ተወሰነ። በታችም ሳይጨመርበት ተወለደ።

He was conceived in the womb without letting there be any place that was not full of Him, He was bound in the womb without making subtraction above, and was born without making addition beneath.

ዲያቆን (Deacon)

ውስተ ጽባሕ ነጽሩ።

ወደ ምሥራቅ ተመልከቱ።

Look to the east.

ካህን (Priest)

ኮነ ሰብአ ፍጹመ ዘእንበለ ኃጢአት ፤ ወአስተርአየ ከመ ገብር እንዘ ይገብር ከመ እግዚአብሔር ፤ በከመ ስምዐ ኮኑ ሰባክያነ ወንጌሉ።

ከኃጢአት በቀር ፈጽሞ ሰው ሆነ። እንደ እግዚአብሔር እየሠራ እንደባርያ ታየ። ወንጌሉን ያስተማሩ እንደመሰከሩ።

He became man, absolutely without sin, and appeared like a servant, working like God, as the preachers of His gospel witnessed.

ዲያቆን (Deacon)

ንነጽር።

እናስተውል።

Let us give heed.

ካህን (Priest)

እምኀበ አቡሁ ተሰብሐ ፤ ወእምኀበ መላእክት ተአኰተ ፤ እምኀበ ሰብእ ተወደሰ ፤ ወእምኀቤሁ ተቀደሰ።

ከአባቱ ዘንድ ተመሰገነ። ከመላእክትም ዘንድ ተመሰገነ። ከሰውም ዘንድ ተመሰገነ ፤ ከራሱም ከበረ።

He was glorified by His Father, He was given thanks by the angels, He was praised by men and sanctified by Himself.

ወመልዐ ሰማያተ ወምድረ ቅድሳተ ስብሓቲሁ ፤ ወዘልፈ እንከ ንሕነኒ ኢነዐርፍ በአልባቢነ ወናነብብ ቅድሳተ ስብሓቲሁ ፤ ወንጸርሕ እንዘ ንብል ቅዱስ።

የጌትነቱም ምስጋና በሰማይና በምድር መላ። እኛም እንግዲህ በልቡናችን ዘወትር አናርፍም። ቅዱስ እያልንም የጌትነቱን ምስጋና እንናገራለን።

The holiness of His glory filled heaven and earth. Henceforth, at all times, we give our hearts no rest but speak of the holiness of His glory and cry saying : Holy, Holy, Holy, perfect Lord of hosts, heaven and earth are full of the Holiness of His glory.

ዲያቆን (Deacon)

አውሥኡ።

ተሰጥኦውን መልሱ።

You answer.

ሕዝብ (People)

ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ እግዚአብሔር ጸባዖት ፍጹም ምሉዕ ሰማያተ ወምድረ ቅድሳተ ስብሐቲከ።

ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ ፍጹም አሸናፊ እግዚአብሔር የጌትነትህ ምስጋና በሰማይ የመላ ነው።

Holy Holy Holy, perfect Lord of hosts, heaven and earth are full of the Holiness of Your Glory.

ካህን (Priest)

ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ አንተ ዘበአማን ኢየሱስ ክርስቶስ ዘትትቄደስ በአፈ ኵሉ።

በሁሉ ፍጥረት የምትመሰገን እውነተኛ ኢየሱስ ክርስቶስ አንተ ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ ነህ።

Truly Holy, Holy, holy are You, Jesus Christ, Who is sanctified by the mouths of all,

ወለኵሎሙ ቅዱሳኒሁ በሠናያቲሁ ወሀቦሙ ከመ ይኩኑ ቅዱሳነ። እንተ ይእቲ ቅድሳቱ እንተ ኢትትነሠት ወኢትማስን። ዘዓይን ኢርእየ ወእዝን ኢሰምዐ ውስተ ልበ ሰብእ ዘኢተሐለየ

ለቅዱሳኑም ሁሉ በቸርነቱ ቅዱሳን ይሆኑ ዘንድ ሰጣቸው። ይህችውም የማትፈርስ ፤ የማትጠፋ ቅዱሳቱ ናት። ዐይን ያላየው ጆሮ ያልሰማው በሰው ልቡና ያልታሰበ

and Who, through His goodness, has granted to all His Holy ones to be Holy. His holy things cannot be destroyed or perish, those things which eye has not seen, nor ear heard, neither have entered into the heart of man,

ዘአስተዳለወ እግዚአብሔር ለእለ ያፈቅርዎ ለአርዳኢሁ ቅዱሳን ወለሐዋርያቲሁ ንጹሓን አርአዮሙ ሥርዓተ ምሥጢር ዘቊርባን።

እግዚአብሔር ለወዳጆቹ ያዘጋጀው ፤ ለቅዱሳን ደቀመዛሙርቱ ለንጹሓንም ሐዋርያት የቊርባን ምሥጢር ሥርዓትን አሳያቸው።

which God has prepared for His Holy disciples and pure apostles who loved Him; and He has shown them the order of the Holy communion.

ዲይቆን (Deacon)

አንሥኡ እደዊክሙ ቀሳውስት።

ቀስውስት እጆቻችሁን አንሡ።

Priests, raise up your hands.

ካህን (Priest)

ነሥአ ኅብስተ በእደዊሁ ቅዱሳት ወብፁዓት እለ እንበለ ርስሐት።

ነውር በሌለባቸው ቅዱሳት ብፁአት በሚሆኑ እጆቹ ኅብስቱን አንስቶ ያዘ።

He took bread in His Holy, blessed and spotless hands.

ሕዝብ (People)

ነአምን ከመ ዝንቱ ውእቱ በአማን ነአምን።

ይህ እንደ ሆነ በእውነት እናምናለን።

We believe that this is He, truly. we believe>

ካህን (Priest)

አንቃዕደወ ሰማየ ኀቤከ ኀበ አቡሁ እግዚአብሔር ወእግዚአ ኵሉ ዘመልዕልተ ኵሉ። አእኰተ ባረከ ወፈተተ

የሁሉ በላይና የሁሉ ጌታ እግዚአብሔር ወደ ሆንህ ወደ አንተ ወደ አባቱ አቅንቶ አየ። አምሰገነ ባረከ ቆረሰ።

He looked up to heaven towards You, His Father, God and Lord of all, Who is above all, gave thanks, blessed and broke.

ወወሀቦሙ ለአርዳኢሁ ወይቤሎሙ ዝውእቱ ሥጋየ መብልዐ ጽድቅ ዘበአማን ዘበልዐ እምኔሁ ቦ ሕይወት ዘለዓለም ንሥኡ ብልዑ እምኔሁ።

"እውነተኛ የጽድቅ ምግብ ሥጋዬ ይህ ነው ብሎ ለደቀመዛሙርቱ ሰጣቸው። ከርሱ የበላ የዘላለም ሕይወት አለው ንሡ ከርሱ ብሉ" አላቸው።

and gave it to His disciples and said to them, "This is My body, which is indeed the food of righteousness ; whoever eats of it has eternal life. Take, eat of it."

## ሕዝብ (People)

አሜን አሜን አሜን ነአምን ወንትአመን ንሴብሐከ ኦ እግዚእነ ወአምላክነ። ከመ ዝንቱ ውእቱ በአማን ነአምን።

አሜን አሜን እናምናለን። እንታመናለን። ጌታችንና አምላካችን እናመሰግንሃለን። ይህ እርሱ እንደሆነ በእውነት እናምናለን።

Amen amen amen: We believe and confess, we glorify You, O our Lord and our God; that this is He we truly believe.

## ካህን (Priest)

ወከማሁ ጽዋዐኒ ቶስሐ ማየ ወወይነ አእኰተ ወቀደሰ ወወሀቦሙ ለአርዳኢሁ ወይቤሎሙ ዝ ውእቱ ደምየ ስቴ ሕይወት

እንዲሁም ጽዋውን ውኃና ወይኑን ቀላቅሎ አመሰገነ ፤ ባረከ ፤ አከበረ። "እውነተኛ የሕይወት መጠጥ ደሜ ይህ ነው" ብሎ ለደቀመዛሙርት ሰጣቸው።

And likewise also the cup mixing water with wine, He gave thanks, blessed sanctified, gave it to His disciples and said to them "This is My blood which is indeed the drink of life,

ዘበአማን ዘሰትየ እምኔሁ ቦ ሕይወት ዘለዓለም ንሥኡ ስትዩ እምኔሁ ኵልክሙ።

“ከርሱ የጠጣ የዘላለም ሕይወት አለው። ሁላችሁ ንሡ ከርሱ ጠጡ” አላቸው።

whoever drinks of it has eternal life: take, drink you all of it.”

ሕዝብ (People)

አሜን አሜን አሜን ነአምን ወንትአመን ንሴብሐከ ኦ እግዚእነ ወአምላክነ። ከመ ዝንቱ ውእቱ በአማን ነአምን።

አሜን አሜን እናምናለን። እንታመናለን። ጌታችንና አምላካችን እናመሰግንሃለን። ይህ እርሱ እንደሆነ በእውነት እናምናለን።

Amen amen amen: We believe and confess, we glorify You, O our Lord and our God; that this is He we truly believe.

ካህን (Priest)

ተአምር ውእቱ ለክሙ ወለእለ እምድኅሬክሙ ወከመዝ ግበሩ ተዝካርየ እስከ እመጽእ። ትትጋብኡ በስምየ ዜንዉ ሞትየ ወትንሣኤየ ፤ ወዕርገትየ ውስተ ሰማያት።

“ለናንተ ከናንተም በኋላ ለሚነሡት ምልክት ነው። መታሰቢያዬንም እንዲህ አድርጉ። እስክመጣ ድረስ በእኔ ስም በምትሰበሰቡበት ጊዜ ሞቴንና ትንሣኤዬን ወደ ሰማይ ማረጌን ንገሩ።”

“It is a sign to you and to those who will come after you, so do likewise in remembrance of Me until I come. Whenever ye gather in My name, proclaim My death, My resurrection and Mine ascension into the heavens.”

ንዜኑ ሞተከ እግዚኦ ወትንሣኤከ ቅድስተ ነአምን ዕርገተከ ወዳግመ ምጽአተከ ንሴብሐከ ወንትአምነከ ንስእለከ ወናስተበቍዐከ ኦ እግዚእነ ወአምላክነ።

አቤቱ ሞትህንና ቅድስት ትንሣኤህን እንናገራለን። ዕርገትህን ዳግመኛም መምጣትህን እናምናለን ፤ እናመሰግንሃለን ፤ እናምንሃለንም። ጌታችንና አምላካችን ሆይ እንለምንሃለን እንማልድሃለንም።

We proclaim Your death, Lord, and Your holy resurrection; we believe in Your ascension and Your second advent. We glorify You, and confess You, we offer our prayer unto You and supplicate You, O our Lord and our God.

ካህን (Priest)

ወንሕነኒ እለ ተጋባእነ ንዜኑ ሕማሞ ለዘኢየሐምም ንዜኑ ሞቶ ለዘኢይመውት፤

የተሰበሰብን እኛም የማይታመም የእርሱን ሕማሙን እንናገራለን ፤ የማይሞት የእርሱን ሞቱን እንናገራለን።

And we, who have gathered together, proclaim the sufferings of Him who does not suffer and proclaim the death of Him who does not die.

በይእቲ ሌሊት እንተ ባቲ ረፈቀ ምስለ አርዳኢሁ መጠወ ነፍሶ ለሞት በፈቃደ አቡሁ ወበሥምረተ ርእሱ።አኀዝዎ ለአኃዜ ኵሉ አሠርዎ ለመላኬ ኵሉ ወሐምይዎ ለወልደ አምላክ ሕያው።

ከደቀመዛሙርቱ ጋራ በተቀመጠባት በዚያች ሌሊት በአባቱ ፈቃድ በራሱም ፈቃድ ሰውነቱን ለሞት ሰጠ። ሁሉን የያዘውን ያዙት። ሁሉን የሚገዛውን አሠሩት። የሕያው የአምላክን ልጅ አሠሩት።

In the same night when He sat with His disciples He gave His soul over to death with the will of His Father and in His own good pleasure. They took hold of Him who takes hold of all, bound the ruler of all and shackled the Son of the living God;

ሰሐብዎ በመዓት ፤ ወተለዎሙ በፍቅር ፤ ወወሰድዎ እንዘ የሐውር ድኅሬሆሙ ከመ በግዕ የዋሕ ዘኢይነብብ በቅድመ ዘይቀርፆ።

በቍጣ ጐተቱት። በፍቅር ተከተላቸው። በሚሸልተው ፊት እንደማይናገር እንደ የዋሕ በግ በኋላቸው እየተከተለ ወሰዱት።

they drew Him in wrath and He followed them in love, they took Him and He followed them like a meek sheep which is dumb before its shearers.

አቀምዎ ውስተ ዐውድ ለዘሎቱ ይቀውሙ ሊቃነ መላእክት በፍርሃት ወበረዓድ ፤ አርስሕዎ ለዘየኀድግ ኃጢያተ ወኰነንዎ ለመኰንነ መኳንንት።

ሊቃነ መላእክት በመፍራትና በመንቀጥቀጥ ከፊቱ የሚቆሙለትን በአደባባይ አቆሙት። ኃጢአትን ይቅር የሚለውን ኃጥእ አሉት። በመኳንንት በሚፈርደው በእርሱ ፈረዱበት።

They caused to stand in the court Him, before whom stand archangels in fear and trembling. He who forgives sins, was accused as a sinner by them, the Judge of judges was judged by them.

ወአስተቀጸልዎ አክሊለ ዘሦክ ለዘያስተቄጽሎሙ ጌራ ለሱራፌል ፤ አልበስዎ ከለሜዳ ዘለይ ለተሣልቆ ለዘያለብሶሙ ሞጣሕተ ግርማ ለኪሩቤል።

ለሱራፌል ዘውድ የሚያቀዳጃቸውን የእሾህ ዘውድ አቀዳጁት። ለኪሩቤል የግርማ ልብስ የሚያለብሳቸውን ለመዘበት ቀይ ግምጃ አለበሱት።

Him, who crowns seraphim with a coronet, they crowned with a crown of thorns. Him, who clothes cherubim with garments of might, they clothed with a scarlet robe to mock Him.

ገብር እኩይ አጽንዐ እዴሁ ወጸፍዖ ገጾ ፤ ለዘይሜወሩ እምቅድመ ገጹ ኪሩባዊያን በአክናፈ እሳት እንዘ ይትገለበቡ።

ኪሩቤል በእሳት ክንፍ ተሸፍነው ከፊቱ የሚሠወሩለትን እርሱን ክፉ ባርያ እጁን አጽንቶ ፊቱን ጸፋው።

A wicked servant strengthened his hand to strike the face of Him from Whose face the cherubim are hidden being covered with wings of fire.

አስተብረኩ ቅድሜሁ እንዘ ይዘነጕግዎ ለዘሎቱ ይሰግዱ ሠራዊተ መላእክት በዐቢይ ድንጋጼ።

የመላእክት ሠራዊት በፍጹም መደንገጥ ለሚሰግዱለት እየዘበቱበት በፊቱ ተንበረከኩ።

They knelt before Him, mocking Him Whom the hosts of angels worship in great fear.

ኦ ትሕትና ዘመጠነዝ ትሕትና። ኦ ትዕግሥት ዘመጠነዝ ትዕግሥት። ኦ አርምሞት ዘመጠነዝ አርምሞት። ኦ ኂሩት ዘመጠነዝ ኂሩት ኦ ፍቅር ዘመጠነዝ አፍቅሮተ ሰብእ።

ይህን ያህል ትሕትና እንደምን ያለ ትሕትና ነው። ይህን ያህል ትዕግሥት እንድምን ያለ ትዕግሥት ነው። ይህን ያህል ዝምታ እንደምን ያለ ዝምታ ነው። ይህን ያህል ቸርነት እንደምን ያለ ቸርነት ነው። ይህን ያህል ሰውን ማፍቀር እንደምን ያለ ፍቅር ነው።

Oh what humility is this! Oh what patience is this! Oh what a silence is this! Oh what a kindness is this! Oh what a love of man is this!

ፍቅር ሰሐቦ ለወልደ አምላክ እመንበሩ ፤ ወአብጽሖ እስከ ለሞት። ሰቀልዎ ከመ እቡስ ለዘአልቦቱ አበሳ ወኈለቍዎ ምስለ ጊጉያን ለገባሬ ሕይወት።

ፍቅር የአምላክን ልጅ ከዙፋኑ ሳበው። እስከ ሞትም አደረሰው። በደል የሌለበትንም እንደ በደለኛ ሰቀሉት። ሕይወትን የሠራውን ከበደለኞች ጋራ ቆጠሩት።

Love drew down the Son of God from His throne and brought Him unto death. Him, who had no wickedness, they crucified as wicked. Him, who is the maker of life, they numbered with the wicked.

ኦ አእዳው እለ ለሐኳሁ ለአዳም ተቀነዋ በቅንዋተ መስቀል። ኦ አእጋር እለ አንሶሰዋ ውስተ ገነት ተቀነዋ በቅንዋተ መስቀል።

አዳምን የፈጠሩ እጆች በመስቀል ቀኖት ተቸነከሩ ወዮ። በገነት የተመላለሱ እግሮች በመስቀል ቀኖት ተቸነከሩ ወዮ።

Oh the hands which formed Adam were nailed with the nails of the cross. Oh the feet which walked in the garden were nailed with the nails of the cross.

ኦ አፍ ዘነፍሐ ውስተ ገጹ ለአዳም መንፈሰ ሕይወት ብሒዐ መጺጸ ዘምስለ ሐሞት ሰረበ።

በአዳም ፊት የሕይወት መንፈስን እፍ ያለ አፍ ከሐሞት ጋራ የተቀላቀለ የኮመጠጠ መጻጻን ጠጣ ወዮ።

Oh the mouth which breathed the spirit of life into the nostrils of Adam drank vinegar mixed with gall.

አይ አፍ ወአይ ከናፍር ወአይ ልሳን ዘይትናገር ሕማማቲሁ ለወልድ። ልብ ይትከፈል ወኅሊና ይዘበጥ ወነፍስ ትርዕድ ወሥጋ ይደክም ሶበ ይትነገር ሕማማቲሁ ለፍቁር።

የወልድን መከራ የሚናገር ምን አፍ ነው? ምን ከንፈር ነው፣ ምንስ አንደበት ነው? የፍቁር የጌታ ሕማማት በተነገረ ጊዜ ልብ ይለያል። ኅሊናም ይመታል። ነፍስም ትንቀጠቀጣለች። ሥጋም ይደክማል።

What mouth, what lips, what tongue can express the sufferings of the Son? The heart is broken, the mind is perplexed, the soul trembles and the flesh is weary when the sufferings of the Beloved are mentioned.

ሞተ ዘኢይመውት ፤ ሞተ ከመ ይሥዐሮ ለሞት፤ ሞተ ከመ ያሕይዎሙ ለሙታን።

የማይሞተው ሞተ። ሞትን ይሽረው ዘንድ ሞተ። ሙታንን ያድናቸው ዘንድ ሞተ።

The Immortal died: died to destroy death, died to quicken the dead.

ዲያቆን (Deacon)

ብክይዎ ወላህውዎ እለ ታፈቅርዎ።

የምትወዱት ሰዎች ፈጽሞ አልቅሱለት።

You who love Him, weep and mourn over Him.

*ካህኑን በመከተል እንበል።* - *Repeat after the priest.*

ዬ ዬ ዬ አማኑኤል አምላክነ።
ዬ ዬ ዬ ኢየሱስ መድኃኒነ።
ዬ ዬ ዬ ክርስቶስ ንጉሥነ።

ወየው ወየው ወየው አማኑኤል አምላካችን።
ወየው ወየው ወየው መድኃኒታችን ኢየሱስ።
ወየው ወየው ወየው ንጉሣችን ክርስቶስ።

ye' ye' ye' Emmanuel our God.
ye' ye' ye' Woe! Jesus our Saviour.
ye' ye' ye' Christ our King.

ካህን (Priest)

ዬ ዬ ዬ አውረድዎ እምዕፅ ዕደው ጻድቃን ወአምጽኡ አፈዋተ ከርቤ ሐውሰ ወልብሰ ገርዜን ንጹሐ ለግንዘተ ሥጋሁ።

ወየው ወየው ወየው ጻድቃን ከዕንጨት አወረዱት። ሥጋውንም ለመገነዝ ከርቤ የሚባል የጣፈጠ ሽቱንና ንጹሕ በፍታ አመጡ።

Ye’ ye’ ye’ the righteous men took Him down from the tree, brought a mixture of myrrh and aloes and pure fine linen cloths to wrap His body.

ሕዝብ (People)

ቅዱስ እግዚአብሔር፤ ቅዱስ ኃይል፤ ቅዱስ ሕያው ዘኢይመውት። ዘተወልደ እማርያም እምቅድስት ድንግል ተሣሃለነ እግዚኦ።

ቅዱስ እግዚአብሔር ቅዱስ ኃያል ቅዱስ ሕያው የማይሞት። ከድንግል ማርያም የተወለደ አቤቱ ይቅር በለን።

Holy God, Holy Mighty, Holy Living, Immortal, Who was born from the Holy Virgin Mary, have mercy upon us, Lord.

ቅዱስ እግዚአብሔር፤ ቅዱስ ኃይል፤ ቅዱስ ሕያው ዘኢይመውት። ዘተጠምቀ በዮርዳኖስ ወተሰቅለ ዲበ ዕፀ መስቀል ቅዱስ ተሣሃለነ እግዚኦ።

ቅዱስ እግዚአብሔር ቅዱስ ኃያል ቅዱስ ሕያው የማይሞት። የማይለወጥ በዮርዳኖስ የተጠመቀ በእንጨት መስቀልም የተሰቀለ አቤቱ ይቅር በለን።

Holy God, Holy Mighty, Holy Living, Immortal, Who was baptized in Jordan and crucified on the tree of the cross, have mercy upon us, Lord.

ሕዝብ (People)

ተዘከረነ እግዚኦ በውስተ መንግሥትከ። ተዘከረነ እግዚኦ ኦ ሊቅ በውስተ መንግሥትከ። ተዘከረነ እግዚኦ በውስተ መንግሥትከ።

አቤቱ በመንግሥትህ አስበን። ሊቅ ሆይ አቤቱ በመንግሥትህ አስበን። አቤቱ በመንግሥትህ አስበን።

Remember us, Lord, in Your kingdom; remember us, Lord, Master, in Your kingdom; remember us, Lord, in Your kingdom,

በከመ ተዘከርኮ ለፈያታዊ ዘየማን እንዘ ሀሎከ ዲበ ዕፀ መስቀል ቅዱስ።

ቅዱስ በሚሆን በዕፀ መስቀል ላይ ሳለህ ፈያታዊ ዘየማንን እንዳሰብከው አቤቱ በመንግሥትህ አስበን።

as You did remember the thief on the right hand when You were on the tree of the Holy Cross.

ካህን (Priest)

አመ ሣልስት ዕለት ሦጣ ለነፍሱ ውስተ ሥጋሁ።

በሦስተኛው ቀን ነፍሱን ከሥጋው ጋራ አዋሓዳት።

On the third day He restored His soul into His body.

ሕዝብ (People)

ቅዱስ እግዚአብሔር፤ ቅዱስ ኃይል፤ ቅዱስ ሕያው ዘኢይመውት ዘተንሥአ እሙታን አመ ሣልስት ዕለት።

ቅዱስ እግዚአብሔር ቅዱስ ኃያል ቅዱስ ሕያው የማይሞት የማይሞት የማይለወጥ በሦስተኛው ቀን ከሙታን ተለይቶ የተነሣ።

Holy God, Holy Mighty, Holy Living, Immoral, who rose from the dead on the third day,

ዐርገ በስብሐት ውስተ ሰማያት ወነበረ በየማነ አቡሁ ዳግመ ይመጽእ በስብሐት ይኰንን ሕያዋነ ወሙታነ ተሣሃለነ እግዚኦ።

በክብር በምስጋና ወደሰማይ ዐረገ በአባቱም ቀኝ ተቀመጠ ዳግመኛም በጌትነት ይመጣል በሕያዋንና በሙታን ለመፍረድ አቤቱ ይቅር በለን።

ascended into heaven in glory, sat at the right hand of His Father and again will come in glory to judge the living and the dead, have mercy upon us, Lord.

ስብሐት ለአብ ስብሐት ለወልድ ስብሐት ለመንፈስ ቅዱስ ይእዜኒ ወዘልፈኒ ወለዓለም ዓለም አሜን ወአሜን ለይኩን ለይኩን።

ለአብ ምስጋና ይሁን ለወልድ ምስጋና ይሁን ለመንፈስ ቅዱስ ምስጋና ይሁን ዛሬም ቢሆን ሁል ጊዜም ቢሆን ለዘላዓለሙ አሜን ይሁን ይሁን ይደረግ።

Glory be to the Father, glory be to the Son, glory be to the Holy Spirit, both now and ever, and world without end. Amen and amen, so be it, so be it.

ካህን (Priest)

ተንሥአ እሙታን ፍጹመ ዘእንበለ ሙስና ወአግዐዘነ እምዐርዑተ ኃጢአት። በይእቲ ሥጋ ምስለ ኃይለ መለኮት ውስተ ሰማያት ዐርገ ኀበ ዘትካት ህላዌሁ።

ሙስና ሳይኖርበት ከሙታን ተለይቶ ፈጽሞ ተነሣ። ከኃጢአት ቀንበርም ነጻ አደረገን። በዚያች ሥጋ በመለኮት ኃይል ወደ ሰማይ ወደ ቀድሞ አኗኗሩ አረገ።

He rose from the dead, absolutely without corruption and set us free from the yoke of sin. In this body, with the power of His divinity, He ascended into heaven to His accustomed position.

ዲያቆን (Deacon)

አድንኑ አርስቲክሙ ቅድመ እግዚአብሔር።

እራሳችሁን በእግዚአብሔር ፊት ዝቅ ዝቅ አድርጉ።

Bow your heads before God:

ካህን (Priest) - በለኖሳስ

ተዘከር እግዚኦ ኪዳን ቃልከ ዘተካየድከ ምስለ አበዊነ ወምስለ ሐዋርያቲከ ቅዱሳን ከመ ትፈኑ ላዕሌነ ውእተ መንፈሰከ ቅዱሰ ዘኢይክል ዓለም ነሢኦቶ።

ከአባቶቻችን ጋራ ከቅዱሳንም ሐዋርያትም ጋራ የተማማልከውን ቃል ኪዳንህን አቤቱ አስብ። ይህ ዓለም መቀበሉን የማይችል ያን መንፈስ ቅዱስህን ለኛ ትሰድልን ዘንድ።

Lord, remember the covenant of Your word which You established with our fathers and with Your holy apostles to send upon us this Your Holy Spirit Whom the world cannot receive.

ወመሀርከነ ለነ ከመ ንጸውዕከ እንዘ ንብል አቡነ ዘበሰማያት ይትቀደስ ስምከ ትምጻእ መንግሥትከ።

በሰማይ ያለህ አባታችን ስምህ ይመስገን መንግሥትህ ትምጣ ብለን እንጠራህ ዘንድ አስተማርከን።

You taught us that we may call upon You saying, Our Father Who are in heaven, hallowed be Your name, Your kingdom come.

ውእቱ ዝኩ መንፈስከ ቅዱስ ዘኢይትፈተን ወዘኢየሐጽጽ። ይምጻእ እምላዕሉ እምሰማየ ሰማያት ልዑል ይባርክ ዘንተ ኅብስተ።

የማይመረመርና ህፀፅ የሌለበት ይኸው መንፈስ ቅዱስህ ልዑል ከሚሆን ከሰማየ ሰማያት ከወደላይ ይምጣ። ይህን ኅብስት ይባርክ ዘንድ።

May this Holy Spirit, who is neither searchable nor inferior, come from above the highest heaven to bless this bread

ወጽዋዐኒ ይቀድስ ይረስዮ ለዝንቱ ኅብስት ሱታፌ ሥጋከ ማሕየዊ። ወካዕበ ይረስዮ ለዝንቱ ጽዋ ሱታፌ ደምከ መስተሣህል።

ጽዋውንም ያከብር ዘንድ ፤ ይህንን ኅብስት ከማሕየዊ ሥጋህ ጋራ አንድ ያደርገው ዘንድ። ዳግመኛም ይህንን ጽዋ ይቅር ባይ ከሚሆን ደምህ ጋራ አንድ ያደርገው ዘንድ።

and to hallow the cup, to make this bread the communion of Your life-giving body and also to make this cup the communion of Your merciful blood.

ሕዝብ (People)

አሜን እግዚኦ መሐረነ ፤ እግዚኦ መሐከነ ፤ እግዚኦ ተሣሃለነ።

አቤቱ ማረን ፤ አቤቱ ራራልን ፤ አቤቱ ይቅር በለን።

Amen; Lord have pity upon us, Lord spare us, Lord have mercy upon us.

ዲያቆን (Deacon)

በኵሉ ልብ ናስተብቍዖ ለእግዚአብሔር አምላክነ ኅብረተ መንፈስ ቅዱስ ሠናየ ከመ ይጸግወነ።

በፍጹም ልብ አምላካችንን እግዚአብሔርን እንማልደው ፤ ያማረ የመንፈስ ቅዱስን አንድነት ይሰጠን ዘንድ።

With all the heart let us beseech the Lord our God that he grant unto us good communion of the Holy Spirit.

ሕዝብ (People)

በከመ ሀሎ ህልወ ወይሄሉ ለትውልደ ትውልድ ለዓለመ ዓለም።

በፊት እንደነበረ ለዘለዓለሙ ለልጅ ልጅም ይኖራል።

As it was, is and shall be unto generations of generations, world without end.

ካህን (Priest)

ይደመር ምስለ ዝንቱ ኅብስት ወጽዋዕ ይኩን ለቅዱሳት ወለአንጽሖ እምርስሐት ወለትንሣኤ እሙታን ለርስተ መንግሥተ ሰማያት ወለሕይወት ዘለዓለም።

ከዚህ ኅብስትና ከወይኑ ጋራ አንድ ይሁን። ለክብር ፤ ከእድፍ ለማንጻት ፤ ከሙታንም ለመነሣት ፤ መንግሥተ ሰማያትን ለመውረስ ፤ ለዘለዓለም ሕይወትም ይሆን ዘንድ።

May He be joined with this bread and this cup that they may be for sanctification, purification from filthiness, resurrection from the dead, inheritance of the kingdom of heaven and everlasting life.

ሕዝብ (People)

አሜን

Amen

ሀበነ ንኅበር በዘዚአከ መንፈስ ቅዱስ ፤ወፈውሰነ ፤ በዝንቱ ቍርስፎራ ፤ ከመ ብከ ንሕየው ዘለኵሉ ዓለም ፤ ወለዓለመ ዓለም።

የአንተ በሚሆን በመንፈስ ቅዱስ አንድ እንሆን ዘንድ በዚሁም በሥጋው በደሙ አድነን። ለዓለሙ ሁሉ በምትሆን በአንተ ለዘለዓለሙ ሕያው እንሆን ዘንድ።

Grant us to be untied through Your Holy Spirit, and heal us by this oblation that we may live in You forever.

ቡሩክ ስሙ ለእግዚአብሔር። ወቡሩክ ዘይመጽእ በስመ እግዚአብሔር። ወይትባረክ ፤ ስመ ስብሐቲሁ ፤ ለይኩን ፤ ለይኩን ፤ ቡሩከ ለይኩን። ፈኑ ፀጋ መንፈስቅዱስ ላዕሌነ።

የእግዚአብሔር ስሙ ምስጉን ነው። በእግዚአብሔር ስም የሚመጣውም ምስጉን ነው ፤ ጌትነቱም ይመስገን ይሁን ይመስገን ይሁን። የመንፈስ ቅዱስ ጸጋን ላክልን።

Blessed be the name of the Lord, and blessed be He that cometh in the name of the Lord, and Let the name of His Glory be blessed. So be it, so be it, so be it blessed. Send the grace of the Holy Spirit upon us.

ዲያቆን (Deacon)

ተንሥኡ ለጸሎት።

ለጸሎት ተነሡ።

Stand up for prayer.

ሕዝብ (People)

እግዚኦ ተሣሃለነ።

አቤቱ ይቅር በለን።

Lord have mercy upon us.

ካህን (Priest)

ሰላም ለኵልክሙ።

ሰላም ለሁላችሁ ይሁን።

Peace be unto you all.

ሕዝብ (People)

ምስለ መንፈስከ።

ከመንፈስህ ጋራ።

And with Your spirit

# ጸሎተ ፈትቶ

## የመፈተት ጸሎት

## " Prayer Of Fraction"

ካህን (Priest)

ወካዕበ ናስተበቊዕ ዘኵሎ ይእኅዝ እግዚአብሔር አብ ለእግዚእ ወመድኃኒነ ኢየሱስ ክርስቶስ። ኦ ዝንቱ ምሥጢር ዘኢይትፌከር ወዘኢይተረጐም።

ዳግመኛ ሁሉን የሚይዝ የጌታና የመድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስን አባት እግዚአብሔርን እንማልዳለን። ወዮ ይህ ምስጢር ፈጽሞ የማይተረጐም ነው።

Again we supplicate the almighty God, Father of our Lord and Saviour. Jesus Christ. Oh this mystery cannot be solved or interpreted!

መኑ ስሙ ወመኑ ስመ አቡሁ አይቴ ብሔሩ ወመኑ የአምር መካነ ማኅደሩ። ኢይክል ሕሊና ልብ አዕሚቆ ወሐሊዮ ከመ ይርከብ ምክንያተ ነገር ወይንግር ኩነቶ ኢዘቀዳሚ ወኢዘደኃሪ።

